# <u>ደርዝ የለሽ ቅስቀሳ፣ ውል አልባ ፖለቲካ</u>

*ከፀሐዬ ደባልቀው*
*<u>ዋሽንግተን ዲሲ</u>*

" The game of politics has absolutely nothing to do with the truth of anything. It is about managing and manipulating how issues are perceived."

አምባገነኖች ለውጥን እንደ ጦር ይፈሩታል እናም ለውጥ አመንጪውንና አራማጁን በተጨባጭ ሃሳብና ፖሊሲ ዙሪያ የመሞገት አቅሙ ስለሚከዳቸው በጭፍን ጥላቻና አሉባልታ ዙርያ አቧራ መቀስቀስን ይመርጣሉ:: የጉዳዩ ጭብጥ ዛቢያውን እንዲስት በማድረግም የአፍዝ አደንዝዝ ፍቱን ተሞክሮአቸውን በመጠቀም የአደባባዩን በጆሮ ሹክሹክታ እንዲሉ እየቀነጨቡ ሲቸበችቡ ፍርሃትንና ስጋትን በማጫር ምልዓተ ሕዝቡ ዘንድ የርዕደትና የጥርጣሬ መንፈስ እየዘሩ የተስፋ ዳቦን በመመገብ ለርካሽ ተልእኮአቸው ስኬት በመሳሪያነት ለመጠቀም ሲዳዳቸው የተስተዋለ ሲሆን ለእውንነቱም የማይሸርቡት ሴራ አይኖርም::

ሰሞኑን በዚህ ባለንበት በምድረ አሜሪካ ሃቁ ገና አሁን እየተገለጠላቸው የመጡ የሚመስሉና ከእንቅልፋቸው ሲባንኑ በWhite House የተቀመጡት ኘሬዝዳንት ቀለምና ስም ዛሬ እየታያቸው ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ዓይነት የወጋገን ሩጫ የጀመሩ ቀቢፁ ተስፋ ሪፐብሊካኖች

መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ እንዲሉ የTea party የሣር ቅጠሉ ንቅናቄ ተወካዮች ነን በማለት (Grass Root Movement) ይቀባጥሩ ገብተዋል:: ለጆሮ የሚቀፍ የድህረት አመለካከታቸውን በይፋ አንግበው ባራክ ኦባማ ሙስሊም ነው፣ ሽብርተኛ ነው በWhite House የመሸገ የዘመኑ ኮሙዩኒስት ነው፣ እናም እንቃወመዋለን በማለት ይደሰኩራሉ:: በአሁኑ ጊዜ ኘሬዘዳንቱ ሸንጣቸውን ገትረውና ወገባቸውን ጠበቅ አድርገው የሚሟገቱለት አብዛኛ ውን አሜሪካዊ ከታላላቅ የሥርዓቱ የኢንሹራንስ አፈና አላቆ ፍትሃዊ የጤናና የደህንነት ዋስትና የሚያጎናፅፈው ረቂቅ ሕግ የቆሻሻ ቅርጫት ሲሳይ ሆኖ እንዲቀር ያለ የሌለ እኩይ ኃይላቸውን መሰሪ ተክህኖአቸውን አስተባብረው የሞት የሽረት ትንቅንቅ እያካሄዱበት ይገኛሉ::

ታዲያ ቁምነገሩ ያለው ለምን የኘሬዘዳንቱን አጀንዳ እደምለዓተ ሕዝቡ ሁሉ አልደገፉም የሚለው አይሆንም:: ነገሩ ወዲህ ነው ጉዳዩን የሚቃወሙበት አግባብ እና ዘዬ ከጭብጡ ጋር ተዛምዶ አለመኖሩ እንጂ፣ የባራክ ኦባማ በአንድ ጎናቸው ከአፍሪካዊ አባት መወለዳቸው፣ የባራክ ኦባማ አባት የእስልምና ዕምነት ተከታይ የነበሩ ስለመሆናቸውና ሰውየው የመሃል ስማቸው ሁሴን በሚል መጠሪያ መለየቱ ከኘሬዘዳንቱ ብቃት፣ ችሎታ፣ ትምህርት፣ ክሂሎት፣ አቅምና ተሰጥኦ ጋር ምን ያገናኘዋል? ኘሬዘዳንቱ ይዘውት የተነሱለትና በምረጡኝ ቅስቀሳም ዘንድ ምለዓተ መራጩን ከዳር ዳር ያንቀሳቀሱበት የዲሞክራቲክ ፓርቲው ምሰሶና ማገር ከሆነውና በአሸናፊነት ነጥሮ ከወጣው ፖሊሲ ጋር ምን ያነካካዋል?

እዚህ ላይ እንግዲህ ሁለቱ መንታ መንገዶችን በእውን በአስተውሎት እንድንከታተል በሚጋብዝ መልኩ ነው የፅሁፉ አቀራረብ:: የዚህ መጣጥፍ እሳቤ በመክፈቻው ላይ በእንግሊዝኛው አባባል እንደተጠቀሰው ሁሉ፣ እውነቱን  በመሸሸ ወይም ጥላሸት በመቀባት የሚገኝ ፋይዳ ቢኖር የከሰረና ያከተመለትን ስውር ደባ በማር በተለወሰ ዳባ ጆብኖ በማቅረብ የሕዝብን ድጋፍና አመኔታን ለማትረፍ መሞከር ትርፉ የባሰ ኪሳራን መከናነብ

እንደሆነ ለማመላከትነው:: ሌላው ፋይዳ ግን በሃገራችን በአሁኑ ጊዜ በመካሄድ ላይ ባለው የምርጫ ሂደት ከብዙ ሺህ ማይልስ ርቀት በነፋስ ሽውታ ሃይል የሰማሁት የምርጫ ቅስቀሳ ቅላፄና ድምፀት ከፍ ሲል በአካባቢያችን ከሚደመጠው ቅጥ ያጣ ተቃውሞ ጋር ስለተመሳሰለብኝ በጉዳዩ ላይ አንዳንድ አስተያየት ለመሰንዘር በመከጀሌ ነው::

የTea Party ዓላማ በተቻለ መጠን በማይጨበጥና እርስ በርሱ በሚጣረስ አስተሳሰብ ኘሬዘዳንት ኦባማን ማጥላላትና ጥቀርሻ መቀባት (የአሜሪካንን ክብር የሚያጎድፍ ቢሆንም እንኳ) እንደሆነ ሁሉ የእኛም የአፍሪካ ቀንድ Tea Party ተምሳሌቶች ከየትም አምጪው ዱቄቱን ፍጪው ዓይነት ፍልስፈና ተከታዮች የሕዝብን ቀልብ ለጊዜው ሊስብ ይችላል ብለው ያመኑባቸውን ማረጋገጫ የለሽ ቅጥፈቶችን (የኢትዮጵያን ሃገራዊ ዝናና ክብር የሚጎዳ ቢሆንም እንኳ) ዝባዝንኬ መዘብዘባቸው ሳይታለም የተፈታ የዘመኑ ጉድ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በረዥም ዘመናት ተጋድሎውና በአትንኩኝ ባይነት፣ በአርበኝነት ገድል ያንፀባረቀው ታሪኩ ለነፃነቱና ለማንነቱ ቀናኢና ኩሩ ሕዝብ እንዳልሆነ ሁሉ መላ አምልኳቸው በባዕዳን ድጋፍ ላይ የተንጠላጠለው ድብልቆች የውጭ ኃይል እነሱን እሽኮኮ ብሎ ለምንሊክ ዙፋን እንዲያበቃቸው በቀን ቅዥትና በሌሊት ሕልም የምኞት ፈረሳቸውን ይጋልባሉ:: ከዓይናቸው ይልቅ ለሩቅ አሉባልታ ጆሮ የሚሰጡ፣ የሚጨበጥ የሚዳሰሰውን ጠጣር እውነታን በመርገጥ ስሜታዊነትና ምናባዊነትን ይበልጥ በማመን በሕልም እንጀራ መጥገብን በመምረጥ ግብዝና አምታች ተዋናይነትን በማስቀደም ተራ ድጋፍ ያስገኝልናል የሚሉትን አታሞ ሲደልቁ በእጅጉ ይስተዋላሉ::

ሸርና ሴራ በእጅጉ ከአንድ ሕብረተሰብ፣ ባህል፣ ልምድ፣ ተሞክሮና የዕድገትና ሁሉን አቀፍ ብስለት ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው ብል እውነታውን

አምብዛም መሳት አይሆንብኝም ምክንያቱም አሁን አሁን ከእኛ ሃገር የምረጡኝ ቅስቀሳ መካከል፣ እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል! እንዳለችው የዋህዋ እንስሳ አንዳንድ ፖለቲከኞችም እኛ ከተሸነፍን ምርጫው ለመጭበርበሩ ዓይነተኛና ብቸኛ ማሳያ ነው በማለት ለራሳቸው የሚሰጡትን ግምት በድፍረት ማቅረባቸው በአያሌው ግራሞትን የሚያጭር ሲሆን፣ ጉዳዩ ግን ያለው ይህ ምን የሚሉት የፖሊሲ አማራጭ ነው፣ ምን የሚሉት የመታገያና የተግባር ኘሮግራም ማሳያነው? ምን የሚሉት ራዕይ ነው? ለሚሉት ጭብጦች ምላሽ ሳይሰጥ ወገቤን ብሎ አውላላ ሜዳ ላይ እጅና እግሩ ተሳስሮ የሚቆም ነው:: ይህ ዓይነቱ የምረጡኝ ዘመቻ ፈሊጥ ጭፍንነትን ጋብዞ የመራጩን አእምሮ በማጨለም፣ ልቡን በመድፈን በስሜት እንዲነጉድ የሚገፋፋ ደርዝ የለሽ ቅስቀሳና የሕዝቡን ሚዛናዊ ብይን የመስጠት ብቃትን የሚያጣጥል የንቀትና የሹፈት ፎርሙላ ከመሆን አይዘልም::

ከኘሮግራም፣ ከራዕይና ከፖለቲካ አመለካከት የራቀ ማንኛው የምረጡኝ ቅስቀሳ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ እንዲሉ ያንበሳውን ድርሻ ጨብጫለሁ በሚል ግልብ ዕምነት እንደሚነዳ መገመት አያዳግትም:: ታዲያ! ሕገ መንግሥቱ ሲፀድቅ ኢሠፓ አልነበረም፣ ኢህአፓና ኦነግ አልነበሩም፣ ኦብነግ አልተወከለም ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ አልነበሩም ስለሆነም ሕገ መንግሥቱ ሙሉእ አይደለም በማለት የተከራከሩበት አንድ የተቃዋሚ ፖርቲ እጩ ተመራጭ ምንም እንኳን እሳቸው ራሳቸው በወቅቱ የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽንን በሊቀመንበርነት የመሩ ለመሆናቸው ቢዘነጉትም አሁንም መልዕክቱ እሳቸውን በአጀብ የሚያደምቁ ጥቂት ስብስቦችና ምርጥ ግለሰቦች ይሁንታን ያላካተተ በመሆኑ እርኩስ ከመርአርዮስ ነው እያሉን እንደሆነ ግልፅ ነው:: ይህም የመራጩን ሕዝብ ብቃት የማስተዋልና ሚዛናዊ አስተሳሰብን ዝቅ በማድረግ ራስንና ጥቂት ቅምጥሎችን ከማግዘፍ የመነጨ ስነልቦናዊና ስነ አዕምሮአዊ ወልጋዳነትና ሰንካላነት የወለደው ፈሊጥ ነው::

እውነቱ ያለው ግን ሕገ መንግሥቱ የረቀቀውና የፀደቀው ከጫፍ ጫፍ ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችንና ሕዝቦችን በነቂስ በወከሉ እውነተኛ ልጆች ይሁንታ መሆኑ ላይ ነው:: ከዚህም በላይ ግን ይኸንን ሕዝቡ የዕለት ተዕለት መመሪያውና መሠረታዊ ሰነዱ አድርጎ የተቀበለውንና በእምነትና በተግባር የአንድነቱ ፅናትና የማዕዘን ድንጋይ የሆነውን ሰነድ የሕዝቡን አዕምሮ በመበከል እናናውጠዋለን ብሎ ማሰብ አሁንም አእምሮ ወለድ ልክፍት ከመሆን አልፎ አንዲት ጋት ታህል የሕዝብን ዕምነት መሸርሸር አይችልም ብቻ ሳይሆን ደርዝ የለሽ ቅስቀሳ ውል አልባ ፖለቲካ ከመሆን አይዘልም::